የመዝሙር ክፍል የአሠራር መመሪያ

መግቢያ

መዝሙር ክፍል በሰ/ት/ቤቱ አደረጃጀት መሠረት ከመዝሙር እና ኪነ ጥበባት ክፍል ውስጥ የሚገኝ ንዑስ ክፍል ነው። መዝሙር ንዑስ ክፍል በሰ/ት/ቤቱ ውስጥ የሚገኙ የዝማሬ አገልግሎቶችን በጠቅላላ የሚያስተባበብር እና የሚመራ ክፍል ነው። ለዝማሬ አገልግሎቶች መቃናት እና እድገት ይህንን የአሠራር መመሪያ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

የቃላት መፍቻ

1. **አገልግሎት፡-** በመዝሙር ጥናት ላይ የተሳተፉ ወንድሞች እና እህቶች በጋራ ወይም በተናጠል በመሆን በዐውደ ምሕረት፣ በጉባዔያት፣ በበዓላት የሚያቀርቡት ለአምላክ የሚቀርብ ያሬዳዊ ምስጋና ማለት ነው።
2. **መዝሙር ጥናት፡-** ለአገልግሎት እንዲሁም ለመንፈሳዊ ዕውቀት የሚሆኑ ወቅቱን የጠበቁ ዝማሬዎች የሚጠኑበት በሳምንት ሦስት ቀናት አሊያም ቀናቱ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ሊጨምር ወይንም ሊቀንስ የሚችል መርሓ ግብር ማለት ነው።
3. **ፍቃድ፡-** በመዝሙር ጥናት አሊያም በአገልግሎቶች ላይ መሳተፍ ለማይችሉ አባላት የሚፈጸም ፍቃድን ሁሉ ያጠቃልላል።
4. **አባል፡-** በዝማሬ አገልግሎት ላይ የሚሳተፉ አባላትን ሁሉ ያመለክታል።

የአሠራር መመሪያው ዓላማ

1. በሁሉም በዝማሬ አገልግሎቶች ላይ ያለ አባል በተገቢው እና ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን በጠበቀ መልኩ የዝማሬ አገልግሎቶችን እንዲፈጽም
2. በሰ/ት/ቤታችን የሚገኘውን የዝማሬ አገልግሎት ካለበት ደረጃ ከፍ ለማድረግ እና በአጥቢያው እንዲሁም ከአጥቢያው ወጪ ከሚገኙት ሌሎች ሰ/ት/ቤቶች ልቆ ለመገኘት
3. ለሁሉም አባል ፍትሐዊ የሆነ አሠራርን ለመዘርጋት

አንቀጽ 1

የመዝሙር ክፍል ሥልጣንና ኃላፊነት

1.1. በሰንበት ትምህርት ቤቱ የሚከናወኑ የዝማሬ አገልግሎትን በኃላፊነት ይመራል

1.2. ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን የጠበቁ መዝሙራትን ለሰ/ት/ቤቱ አባላት ያስጠናል

1.3. ስለ ያሬዳዊ መዝሙራት ለሰ/ት/ቤቱ አባላት ትምህርቶች ና ሥልጠናዎች እነዲሰጡ ያደርጋል

1.4. በቤተክርስቲያን ዓበይት ና ንዑሳን /ወርኃዊ / በአላት ላይ አባላትን በማሰልጠን በሰ/ት/ቤቱ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት የዝማሬ አገልግሎት እንዲሰጡ ያደርጋል

1.5. የወረብ፣ የዝማሜ፣የከበሮ እና የዜማ መሳሪያዎች ሥልጠና እንዲሰጡ ያደርጋል

1.6. የሚዘመሩ መዝሙራትን በመለየት በወቅታቸው እንዲዘመሩ ያደርጋል

1.7. አባላት ለክፍሉ ማሳወቅ የሚፈልጉትን ነገር ለምሳሌ ፈቃድ፣ተጨማሪ አገልግሎት ሲኖር አባላቱ በመቀበል እንደክፍል እንዲታወቅ ያደርጋል

አንቀጽ 2

2. አገልግሎትን በተመለከተ

2.1. በቁጥር የሚታወቁ የዝማሬ አገልግሎት የሚቀርብባቸው መርሐ ግብራት

ወራት	ያሉ የበዓላት ዝርዝር		ሰንበታት (በቁጥር)
	ወርኃዊ(ዕለታት)	ዓመታዊ	
መስከረም	5፣ 14፣ 28	• መስቀል	5
ጥቅምት	28	• ጥቅምት 5 • ጥቅምት 14	4
ኅዳር	5፣ 14፣ 28		4
ታኅሣሥ	5፣ 14፣ 28		4
ጥር	14፣ 28	• ጥር 5 /የጌታችን ልደት • ጥምቀት/ ጥር 10 እና 11	4
የካቲት	5፣ 14፣ 28		5
መጋቢት	14፣ 28	• መጋቢት 5	4
ሚያዝያ	5፣ 14፣ 28		4
ግንቦት	5፣ 14	• ግንቦት 11 • ግንቦት 28	4
ሰኔ	5፣ 14፣ 28		5
ሐምሌ	14፣ 28	• ሐምሌ 5	4
ነሃሴ	5፣ 14፣ 28	• ደብረ ታቦር/ ነሃሴ 13	5
ድምር	**31**	**10**	**52**

በጠቅላላው በአንድ ዓመት ውስጥ ቋሚ የሆኑ 31 ወርኃዊ የአገልግሎት ቀናት 10 የሚሆኑ ዓመታዊ ክብረ በዓላት ላይ የሚደረጉ የአገልግሎት ቀናት እንዲሁም 52 ሰንበታት ላይ የሚደረጉ የዝማሬ አገልግሎቶች በሰ/ት/ቤታችን ዘማርያን ይሸፈናሉ። በጠቅላላው በዓመት 93 ቋሚ የአገልግሎት ቀናት ይኖራሉ።

ማሳሰቢያ ፦ የሰንበት አገልግሎት በየዓመቱ 5 እሑድ የሚውልበት ቀን ይቀያየራል።

2.2. በየወቅቱ የሚፈራረቁ የዝማሬ አገልግሎት የሚቀርብባቸው መርሐ ግብራት

- የሠርግ አገልግሎት

- ከሌሎች ደብራት በሚመጡ ደብዳቤዎች የሚቀርቡ ዝማሬዎች (ሙሉ አገልግሎቱን መሸፈን ወይም የተወሰኑ አባላትን በመላክ አገልግሎቱ ላይ ማሣተፍ)
- የምርቃት አገልግሎት
- የንስሀ አባት እና ልጆች ጉባኤያት
- በኪነጥበብ ክፍል የተዘጋጁ መርሃ ግብራት
- እንዲሁም ከተለያዩ ክፍላት በሚጠይቁት ጥያቄዎች የሚቀርቡ አገልግሎቶች

አንቀጽ 3

3. መዝሙር ጥናትን በተመለከተ

3.1. ቋሚ የሆኑ ሦስት የጥናት ቀናት ይኖራሉ። እነዚህም ረቡዕ፣ አርብ እና እሑድ ናቸው። እንደ አስፈላጊነቱም ሌሎች የጥናት ቀናት ይኖራሉ።

3.2. የጥናት ሰዓቱም ከምሽቱ 12፡00 ሰዓት እስከ 2፡00 ብቻ ነው።

3.3. የጥናት አቴንዳንስ ከ12፡30 በኋላ አይያዝም፤ እስከ 12፡45 ድረስ የመጣ አባል አርፋጅ ተብሎ ይያዛል።

3.4. በዕለቱም የተመደቡት መዝሙር የሚያስጠኑ እህቶች ወይም ወንድሞች የእለቱን ጥናት በተፈቀደላቸው ሰዓት ያስጠናሉ።

3.5. የመዝሙር ጥናቱ አራት ምድብ ይኖሩታል።

3.5.1. **ብስድራ ምድብ፦** የቀዳማይ ኮርስን የጨረሱ በሙሉ በዚህ ምድብ ላይ ገብተው ያጠናሉ።

3.5.2. **መንክራ ምድብ** ፦ ከሚከተሉት መመዘኛዎች ውስጥ ሁለቱን የማያሟሉ ከሆነ መንክራ ምድብ ጥናት ውስጥ ገብተው ያጠናሉ።

- የወጣቶችን የዝማሬ አገልግሎት ከጀመሩ 1 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆናቸው
- መዝሙር ጥናት ላይ ከተገኙ 2 ወር እና ከዚያ በታች የሆናቸው
- የካልዓይ ኮርስን ጨርሰው ያጠናቀቁ
- መዝሙር ክፍል የሚያስቀምጠውን መመዘኛ በተገቢው መልኩ አሟልተው የሚያልፉ

3.5.3. **ሳዊሮስ ምድብ** ፦ በላይ ከተዘረዘሩት መመዘኛዎች ውስጥ ቢያንስ ሦስቱን የሚያሟሉ ሳዊሮስ ምድብ ጥናት ውስጥ ገብተው ያጠናሉ።

3.5.4. **ቅዱስ ያሬድ ምድብ ፦** በዚህ ምድብ የሚሳተፉት

- በሳዊሮስ ምድብ ዝማሬው አገልግሎት ላይ እንዲሁም የመዝሙር ጥናት ላይ ተገቢው የአገልግሎት ትጋትና አቴንዳንስ ያላቸው።
- እንዲሁም የሚከተሉትን ሥልጠናዎች የሠለጠኑ ፦
  - በሰንበት ት/ቤቱ መዝሙር ደብተር ላይ ያሉትን መዝሙሮች ያጠኑ
  - መሰረታዊ የሽብሸባ እና እንቅስቃሴ ሥልጠና

- ❖ መሰረታዊ የድምጽ አወጣጥ ሥልጠና
- ❖ የጽፋት ወረብ ሥልጠና
- ❖ የአመላለስ ወረብ ሥልጠና
- ❖ የጎንደር ወረብ /መረግድ/ ሥልጠና
- ❖ የከበሮ ሥልጠና
- ❖ የዝማሜ ሥልጠና
- ❖ የሌሎች የወረብ ይትበሃሎች ስልጠና

- በወረብ እና በዝማሬ አገልግሎት ላይ የነበሩ ምዘናዎችን በሙሉ ያለፉ።

3.4.2. የአራቱም ምድቦች የጥናት ቀን መዝሙር ክፍሉ በሚያወጣው ቀን ይወሰናሉ።

3.4.3. ከአንድ ምድብ ወደ ሌላኛው ምድብ መዘዋወርያው ጊዜ 6 ወር ነው።

3.5. ከብስድራ ምድብ ወደ መንክራ ምድብ ለመዘዋወር

- የካልዓይ ኮርስን ማጠናቀቅ
- በተገቢው መልኩ በጥናቶች ላይ መገኘት ከተገቢው ፍቃድ ቀን ውጪ ከ75 በመቶ በላይ በጥናት ላይ መገኘት

3.6. ከመንክራ ምድብ ወደ ሳዊሮስ ምድብ ለመዘዋወር፡

- በተገቢው መልኩ በጥናቶች ላይ መገኘት ባለፈው 6 ወራት ውስጥ ከተገቢው ፍቃድ ቀን ውጪ ከ75 በመቶ በላይ በጥናት ላይ መገኘት
- በ6 ወራት ውስጥ ያሉትን የተመደቡባቸውን ሁሉንም አገልግሎቶች ከተገቢው ፍቃድ ቀን ውጪ ያገለገሉ
- በምድብ ውስጥ የነበሩ ሥልጠናዎችን በተገቢው መልኩ የሰለጠኑ

3.7. ከሳዊሮስ ምድብ ወደ ቅዱስ ያሬድ ምድብ ለመዘዋወር፡

- በተገቢው መልኩ በጥናቶች ላይ መገኘት ባለፈው 6 ወራት ውስጥ ከተገቢው ፍቃድ ቀን ውጪ ከ75 በመቶ በላይ በጥናት ላይ መገኘት
- በ6 ወራት ውስጥ ያሉትን የተመደቡባቸውን ሁሉንም አገልግሎቶች ከተገቢው ፍቃድ ቀን ውጪ ያገለገሉ
- በምድብ ውስጥ የነበሩ ሥልጠናዎችን በተገቢው መልኩ የሰለጠኑ
- በወረብ እና በዝማሬ አገልግሎት ላይ የነበሩ ምዘናዎችን በሙሉ ያለፉ።
- መዝሙር ክፍል ቋሚ ዘማርያን እንዲሆኑ ያመነባቸው ከሆነ እና በተገቢው መልኩ አንቀጽ 4 ላይ የተጠቀሱትን የሥነ ምግባር መርሆች የተገበሩ ከሆነ

አንቀጽ 4

4. አባላት ዝማሬን በተመለከተ ሊከተሏቸው የሚገቡት ደንቦች

4.1. መዝሙር ጥናት በተመለከተ

4.1.1. ማንኛውም አባል በጥናት ቀን የሚጠኑትን ሁሉንም ጥናቶች በተገቢው መልኩ ማጥናት እንዲሁም ለቀጣይ ቀናት አጥንቶ መምጣት ይጠበቅበታል።

4.1.2. ማንኛውም አባል በጥናት ላይ የመዝሙር ደብተር ይዞ መገኘት ይጠበቅበታል።

4.1.3. ማንኛውም አባል በመዝሙር ጥናት ቀን መቅረት አይችልም፤ በጥናት ቀን የማይችሉ አባላት የፍቃድ ፎርም የመሙላት ግዴታ አለባቸው።

4.1.4. ማንኛውም አባል በመዝሙር ጥናት ቀን ማርፈድ አይችልም፤ በጥናት ቀን የሚያረፍዱ አባላት የፍቃድ ፎርም የመሙላት ግዴታ አለባቸው።

4.1.5. ማንኛውም አባል በመዝሙር ጥናት ላይ ክርስቲያናዊ የሆነ አለባበስ ለብሶ መገኘት አለበት፤ እንዲሁም ጌጣጌጥ (ቀለበት፣ ጆሮ ጌጥ፣ የእጅ አንባር፣ የመሳሰሉትን...) አጭር ነጠላ ለብሶ መገኘት የለበትም።

4.1.6. ማንኛውም አባል በመዝሙር ጥናት ሰዓት መግባት መውጣት፣ ስልክ ማናገር፣ የጎንዮሽ ወሬ ማውራት፣ መሳቅ፣ ሳይፈቀድ ማውራት አይቻልም።

4.1.7. ማንኛውም አባል በዕለቱ ከመዝሙር ክፍል ተወክሎ የተገኘውን አስተባባሪ ሳያስፈቅድ የመዝሙር ጥናቱን አቋርጦ መውጣት አይችልም።

4.1.8. ማንኛውም አባል ከተመደበበት ምድብ ውጪ ገብቶ ማጥናት አይችልም።

4.2. አገልግሎትን በተመለከተ

4.2.1. ለአገልግሎት የሚያበቁ መስፈርቶች

4.2.1.1. ጥናቱ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ ለአገልግሎቱ የሚያስፈልገውን በቂ የሆነ አቴንዳንስ ማሟላት ይኖርበታል።

4.2.1.2. መዝሙር ክፍሉ የሚያስቀምጠውን መመዘኛ ማለፍ አለበት

4.2.2. በአገልግሎት ላይ

4.2.2.1. ማንም አባል አገልግሎት ያለ አሳማኝ ፍቃድ መቅረት አይችልም።

4.2.2.2. የአገልግሎት ልብስ በሰዓቱ በመገኘት መልበስ ይኖርበታል።

4.2.2.3. በአገልግሎት ሰዓት ከአስተባባሪው ፈቃድ ውጪ ወደየትም ቦታ መንቀሳቀስ አይቻልም።

4.2.2.4. በአገልግሎት ሰዓት ላይ በሌሎች ክፍሎች አማካኝነት ስማቸው ተላልፎ ለሌላ አገልግሎት ከተፈለጉ አባላት ውጪ ከአገልግሎት ሥፍራው መሄድ አይቻልም።

4.2.2.5. ማንኛውንም ዓይነት ጆሮ ጌጥ፤ ሰዓት፤ የእጅ አንባር የመሳሰሉትን ለብሶ ወደ አገልግሎት መውጣት አይቻልም።

4.3. የአገልግሎት መመዘኛ

4.3.1. የዝማሬ አገልግሎት

4.3.1.1. መዝሙሩን ያስጠኑት አስጠኚዎች ከመዝሙር ክፍል ጋር በመተባበር የፈተና ቀን ያዘጋጃሉ። የፈተናውም ቀን ከአገልገልቱ ከ5 እስከ 8 ቀናት ውስጥ መሆን አለበት።

4.3.1.2. ፈተናው ሁለት ነገሮችን ይይዛል። የመዝሙር ዜማን እና የዝማሬ እንቅስቃሴ ናቸው።

4.3.2. ለወረብ አገልግሎት

4.3.2.1. ወረቡን ያስጠኑት አስጠኚዎች ከመዝሙር ክፍል ጋር በመተባበር የፈተና ቀን ያዘጋጃል። የፈተናውም ቀን ከአገልገልቱ ከ5 እስከ 8 ቀናት ውስጥ መሆን አለበት።

4.3.2.2. ወረቡ ሁለት ነገሮችን ይይዛል። የወረብ ዜማ (ቅኝት፣ የጽናጽል ዜማ፣ የቸብቸቦ ዜማ) እና የወረብ እንቅስቃሴ (መቋሚያ አነሳስ፣ ጽናጽል እና መቋሚያ አያያዝ)

4.3.3. መሰረታዊ የበዓሉ ግንዛቤ

4.3.3.1. በዓሉን በተመለከተ ሚመዘነው አባል ሙሉ ዕውቀት ሊኖረው ይገባል

4.4. የአገልግሎት ልብስን በተመለከተ

4.4.1. ማንኛውም አባል ለአገልግሎት ልብስ ተገቢውን ክብር ሊሠጥ ይገባዋል።

4.4.2. በዕለቱ ለአገልግሎት በመዝሙር ክፍል ተወክሎ ከሚያስተባብረው አስተባባሪ ፍቃድ ውጪ የአገልግሎት ልብስ መልበስም ሆነ ማውለቅ አይቻልም።

4.4.3. በአገልግሎት ላይ የአገልግሎት ልብስ ለብሶ ምግብ መመገብ መጠጥ መጠጣት አይቻልም፡ ፡ መመገብ አስፈላጊ ከሆነ የአገልግሎት ልብስ አውልቆ በአግባቡ አስቀምጦ በኋላ ላይ መልበስ ይቻላል።

4.4.4. የአገልግሎት ልብስ ለብሶ ምንም ዓይነት ክርክር፣ ጸብ፣ ከክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ውጪ የሆኑ ነገሮችን መፈጸም አይቻልም።

4.4.5. ማንኛውም አባል ከአገልግሎት ቀን በኋላ የአገልግልት ልብስ በሚታጠብበት ጊዜ ተገኝቶ ማጠብ የግድ ይኖርበታል።

አንቀጽ 5

5. ፍቃድን በተመለከተ

5.1. ማንኛውም አባል ፍርሃተ እግዚአብሔርን ገንዘብ አድርጎ የፍቃድ ፎርምን መሙላት ይችላል። ለእውነተኛነቱም ተገቢውን ማስረጃ ሊያቀርብ ግድ ይላል። የፍቃድ ፎርሙም የቀን እና የሰዓት ነው።

5.2. በሰ/ት/ቤቱ የሚታውቁት የመዝሙር ጥናት ቀናት ውስጥ ሙሉ ለሙሉ ፍቃድ መሙላት አይችልም። ቢያንስ አንድ የመዝሙር ጥናት ቀን ማስቀረት ይኖርበታል።

5.3. የፍቃድ ፎርም በዓመት ሁለት ጊዜ ብቻ ይሞላል፤ የሚሞላውም በጥቅምት እና በመጋቢት ወር ብቻ ነው፤ የመሙያ ጊዜውም ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ ለሦስት ሳምንታት ብቻ ነው።

5.4. ማንኛውም አባል ፍቃድ ባልሞላበት ቀን የሚኖሩ አገልግሎቶች ላይ የመሳተፍ ግዴታ አለበት።

5.5. ማንኛውም አባል ፍቃድ በሞላበት ዕለት የተጠኑ ጥናቶችን በራሱ አጥንቶ የመገኘት ግዴታ አለበት።

5.6. በመጨረሻ የመመዘኛው ጊዜ በፍቃድ ምክንያት ባልነበረበት ዕለታት የተጠኑ መዝሙራት ቢመዘን ቅሬታ ማቅረብ አይችልም።

አንቀጽ 6

6. የቅጣት አወሳሰን በተመለከተ

6.1. ለአገልግሎት ከሚገባው የመዝሙር ጥናት ቀናት ከተገቢው የፈቃድ ቀን ውጪ 75 በመቶውን ያልተገኘ አባል በአገልግሎት ላይ መሣተፍ አይችልም።

6.2. ለሁለት ቀናት መዝሙር ደብተር ይዞ ያልመጣ አባል እንደ አንድ ቀን ቀሪ ይቆጠርበታል።

6.3. በአንቀጽ 4.1.5 እና 4.1.6 ላይ የተጠቀሱትን የመዝሙር ጥናት ደንቦች ሁለት እና ከዚያ ጊዜ በላይ የተላለፈ አባል እንደ አንድ ቀን ቀሪ ይቆጠርበታል።

6.4. ያለ ምንም ፈቃድ አገልግሎት የሚቀር አባል በቀጣይ በሚገኘው አገልግሎት ላይ አይሳተፍም።

6.5. ከአስተባባሪው ፈቃድ ወጪ በአንቀጽ 4.2.2 የተቀመጡትን የአገልግሎት ደንቦች ቢተላለፍ በመጀመሪያ በቃል ማስጠንቀቂያ ይታለፋል፤ ሁለተኛ በጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ይታለፋል፤ በሦስተኛ ግን ከማንኛውም የዝማሬ አገልግሎት እና መዝሙር ጥናቶች ለሁለት ወራት ያክል ይታገዳል፤ በዕገዳው ጊዜ የሚሰጠውን ማንኛውም ዓይነት ቅጣት የመቀበልና የመተግበር ግዴታ ይኖርበታል።

6.6. የአገልግሎት ልብስ በሚታጠብበት ጊዜ ያልተገኘ አባል የአገልግሎት ልብሱን በግሉ ጊዜ አመቻችቶ በቤተክርስቲያን ውስጥ የማጠብ ግዴታ አለበት፤ ይህን ያላደረገ አባል በቀጣዩ ዓመታዊ ክብረ በዓል ላይ አይሳተፍም።

6.7. የሞላው የፍቃድ ፎርም ከእውነተኝነት የራቀ ከሆነ ውድቅ ይሆናል።

ማጠቃለያ

በሰ/ት/ቤቱ መዝሙር ክፍል የተዘጋጀው ይህ የአሠራር መመሪያ መዝሙር ክፍሉ መሻሻል አለበት ብሎ ካመነ ለሰ/ት/ቤቱ ሥራ አመራር አሳውቆ ፍቃድ ካገኘ ብቻ ይሻሻላል፤ እንዲሁም ለሰ/ት/ቤታችን የዝማሬ አገልግሎት እድገት በጣም ወሳኝ ስለሆነ ለተፈፃሚነቱ ሁላችንም ተገቢውን ትብብር እንድናደርግ አምላከ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ይርዳን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር!
ወወላዲቱ ድንግል!
ወለመስቀሉ ክቡር!

አምላከ ገብረ መንፈስ ቅዱስ አገልግሎታችንን ይባርክ!!

ይህ የመዝሙር ክፍል መመሪያ ከዛሬ መጋቢት 13 / 2014 ዓ.ም ጀምሮ በሰ/ት/ቤቱ ጽ/ቤት ጸድቋል።